ספריית פיג'מה

# አየሌት ጉዞ እያደረገች ነው - המשך פעילויות בעקבות הסיפור

በ: ሪናት ሆፐር
ምሳሌዎች: ሪናት ሆፐር
הוֹצָאָה: כנרת זמורה
የእድሜ ክልል: ታዳጊዎች

הַשְׁרָאָה

**ፒንተረስት**

[ተጨማሪ ስራዎች፣ መዝሙሮችና እንቅስቃሴዎች በፒጃማ ቤተ መጻህፍት ፒንተረስት ላይ]

קְרִיאָה

**ምክር ለቤተሰባዊ ንባብ**

ገፀ ባህሪያቱን መግለጽ የታዳጊዎችን የንባብ ልምድ ያሳድጋል፣ ይስባቸዋልና በታሪኩ ላይም እንዲያተኩሩ ይረዳቸዋል። በእያንዳንዱ እንስሳ ላይ የባህሪ ድምጽን ወይም እንቅስቃሴን ማከልና በሚታይበት ጊዜ ሁሉ መድገም ይችላሉ። ለምሳሌ:- ለወፍ እጆችን ማወዛወዝ፣ ለጥንዚዛ አንቴና ወይም ጣቶችዎን እንደ ቀንድ አውጣ ዛጎል በቡጢ ማጣጠፍ።

ሪናት ሆፐር "አትክልተኛው ሃናን" "በበትር ላይ ያለ ደመና" እና ሌሎችንም ጨምሮ የእሥራኤል ክላሲክ የሆኑ የብዙ ተወዳጅ መጽሃፎች ሠዓሊና ደራሲ ነች። የእርሷ ልዩ ዘይቤ በምሣሌነት በፅሁፍና በምስል የተዋሃዱ ሲሆኑ በቀልድ፣ በበለፀገ ቋንቋ፣ በምናብና በግጥም የተሞላ ነው። ለሰፊ ስራዋ ሆፐር ብዙ ሽልማቶችን አግኝታለች።

שִׂיחָה

**በእግር ጉዞ እንስሳትን መገናኘት**

ወደ ቤት በሚሄዱበት ጊዜ በእግር ጉዞ ወይም በአካባቢዎ ስላገኟቸው እንስሳት ማውራት ይችላሉ። በመጽሐፉ ውስጥ ካሉት እንስሳት መካከል አንዱንም አግንታችኋል? ምን ሌሎች እንስሳት አገኛችሁ? እያንዳንዱ እንስሳ የት ነው ?የሚኖረው

שְׁמַע

**QR ኮድ**

አየለት ከዲዲና ከያርዴን ጋር በፒጃማ ቤተ መፃህፍት ፖድካስት ላይም ትጓዛለች። ኮዱን ስካን ያድርጉና... በማዳመጥ !ይደሰቱ

מִשְׂחָק

**ምስላዊ ፍንጮች**

በታሪኩ ውስጥ የእያንዳንዱ እንስሳ ገጽታ በጽሁፉና በምስሉ ውስጥ የመጀመሪያ ፍንጮችን የያዘ ነው። የትኛው እንስሳ ሊመጣ እንደሆነ በእያንዳንዱ ደረጃ ላይ ለመገመት ይሞክሩ። እንዲሁም የግምታዊ ጨዋታ መጫወት ይችላሉ:-
በእያንዳንዱ ጊዜ በቤተሰቡ ውስጥ አንድ ሰው ከመፅሃፉ ውስጥ አንዱን እንስሳ በድምፅና በእንቅስቃሴ ያስመስላል።
የተቀሩት ደግሞ ማን እንደሆነ ለመገመት ይሞክራሉ።

מִשְׂחָק

**የእግር ጉዞ በቤት ውስጥ**

የተለያየ መጠን ያላቸው የእንስሳት አሻንጉሊቶችን በመውሰድ ሁሉንም እንደ አየለት ለመሸከም መሞከርና በቤቱ ውስጥ በእግር መጓዝ ይቻላል። ኪስ ውስጥ የሚገባው ማን ነው? በጭንቅላቱ ላይ የሚቆመውስ ማን ነው? ምናልባትስ ?አየለት እስካሁን ያልሞከረችውን አዲስ መንገድ ታገኙ ይሆን

עוד פעילויות באתר ספריית פיג'מה www.pjisrael.org